የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር - 264951

ሐምሌ 04 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ዋዚሞ ዋሲራ

ሰናይት አድነዉ

አመልካች፡- አቶ ቴዎድሮስ ታምሩ

ተጠሪ፡- 1. አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 1 ቀበሌ 01/02 ዋስትና ሸማቾች ህብረት ሥራ ማህበር

**2.** አራዳ ክ/ከተማ ንግድ ጽ/ቤት

ይህ መዝገብ ለምርመራ ከተያዘዉ ቀጠሮ በፊት ሊቀርብ የቻለዉ አመልካች ሰኔ 21 ቀን 2016 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ እግድ እንዲሰጥ በመጠየቃቸዉ እና በቀረበዉ የእግድ አቤቱታ ላይ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት መዝገቡን መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነዉ።

የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 238199 ላይ ህዳር 27 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 03000210 ላይ መጋቢት 25 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉን ፍርድ አመልካች በመቃወማቸዉ ነዉ። አመልካች ግንቦት 19 ቀን 2016 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ሁለቱ ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚሉባቸዉን ምክንያቶች ዘርዝረዉ በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸዉ ጠይቀዋል። የሰበር አጣሪ ችሎትም የቀረበዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ሰኔ 20 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት ጉዳዩ በሰበር ሰሚ ችሎት እንዲታይ መርቶታል። በዚህም መሠረት መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ትዕዛዝ ተሰጥቷል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1. ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለዉ ለዚህ የአፈፃፀም ክርክር ምክንያት የሆነዉ ዉሳኔ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 174822 ላይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ተጠሪዎች ለአመልካች ሊያስረክቡ ይገባል በማለት የተሰጠ ዉሳኔ ነዉ። በዚህ ዉሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ተጠሪዎች በተናጥል በሁለት የተለያዩ መዛግብት ላይ ይግባኝ አቅርበዋል። ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 281023 ላይ ክርክሩን ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ የሻረ ሲሆን፣ ይህ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል አመልካች ለዚህ ሰበር ያቀረቡት አቤቱታ በሰ/መ/ቁጥር 242253 ላይ ታይቶ ተሰርዟል። በሌላ በኩል ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 281024 ላይ የአሁን 2ኛ ተጠሪ ያቀረበዉን ይግባኝ መርምሮ የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፤ 2ኛ ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 231676 ላይ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ዉሳኔ አጽንቶታል። አመልካች ላቀረቡት አፈፃፀም መሠረት ያደረጉትም ይህንኑ ሲሆን፣ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቀረበዉን

የአፈፃፀም ዳኝነት ዉድቅ ያደረገዉ ሰበር ሰሚ ችሎት ከላይ በተመለከቱት ሁለቱ መዛግብት ላይ የሰጣቸዉ ዉሳኔዎች የሚጣረሱ በመሆኑ ለመፈጸም አስቸጋሪ ነዉ የሚል ይዘት ያለዉ ምክንያት በመስጠት ነዉ፤ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በበኩሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር በመ/ቁጥር 281023 ላይ የሰጠ ዉሳኔ በመ/ቁጥር 281024 ከሰጠዉ ዉሳኔ የበላይነት አለዉ የሚል ምክንያት በመጥቀስ ሲሆን ቢሆንም ዉጤቱ አመልካች ለአፈፃፀም አቤቱታዉ መነሻ ያደረገዉ ዉሳኔ መሠረት ሊፈጸም አይችልም የሚል ይዘት ያለዉ ነዉ። በሌላ በኩል ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ንብረት (ቤት) ተመዝግቦ የሚገኘዉ በአሁን 2ኛ ተጠሪ ስም ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ ይቻላል። ከላይ እንደተመለከተዉ 2ኛ አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ በተናጥል ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበዉ አቤቱታ ዉድቅ ተደርገዉ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ጸንቷል። ይህም 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች ያስረክብ በሚል የተሰጠ ዉሳኔ ጸንቶ ያለ መሆኑን የሚያሳይ ነዉ። ከዚህ ሁሉ አኳያ ሲታይ የስር ፍርድ ቤቶች የቤቱ ስመ ሀብት በስሙ ተመዝግቦ የሚገኝ 2ኛ ተጠሪን አስመልክቶ የተሰጠ ዉሳኔ ጸንቶ ያለ ስለመሆኑ ከግምት ዉስጥ ሳያስገቡ ከላይ የተመለከተዉን ምክንያት በመጥቀስ የአመልካችን የአፈፃፀም አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የሰጡት ዉሳኔ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል።

2. የችሎቱ መጥሪያ ከአመልካች የሰበር አቤቱታ እና ከማስቀረቢያ ነጥቡ ጋር ለተጠሪዎች ደርሶ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክራቸውን በሬጅስትራር በኩል ተቀባብለው ያጠናቅቁ።

3. በአመልካች በቀረበዉ የእግድ አቤቱታ ላይ ተጠሪዎች አስተያየቻቸዉን እንዲያቀርቡ የአቤቱታዉ ግልባጭ ከመጥሪያ ጋር እንዲደርሳቸዉ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 157 መሠረት ታዟል። በእግድ አቤቱታዉ ላይ ተጠሪዎች የሚያቀርቡትን አስተያየት ለመጠበቅ ለሐምሌ **30** ቀን **2016** ዓ.ም ተቀጥሯል።

4. በዋናዉ ጉዳይ ላይ ተጠሪዎች የሚያቀርቡትን መልስ ለመጠበቅ 14/12/2016 ዓ.ም 4፡00 ሰዓት ተቀጥሯል።

ማስታወሻ - ትዕዛዙ የተነበበዉ ሐምሌ 19 ቀን 2016 ዓ.ም ነዉ።

የማይነበብ  የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ **264951**

<u>የ ል ዩ ነ ት ሃ ሳ ብ</u>

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው ለፍርድ አፈጻጸም ክርክር መሰረት የሆነዉ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 174822 ነሐሴ 7/2013 ዓ.ም በዋለ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ነው። የውሳኔው ይዘት የሚያስረዳው የአሁን ተጠሪዎች የቤት ቁጥር 932 የሆነውን ቤት ለቀው ለአመልካች እንዲያስረክቡ መወሰኑን ነው።

በዚህ ውሳኔ ላይ ተጠሪዎች የየበኩላቸውን ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል። 1ኛ ተጠሪ ባቀረበው ይግባኝ ላይ ከአመልካች ጋር ተከራክረው በመ/ቁ 281023 ታህሳስ 13/2014 ዓ.ም በዋለ ችሎት የአሁን አመልካች አከራካሪው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/1967 ያልተወረሰ ነው (የአውራሼ የምርጫ ቤታቸው ነው) በማለት የሚያቀርቡት ክርክር አግባብነት ባለው ማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ ሽሯል። በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ቅር ተሰኝተው በይግባኝ ለፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 221045 ያቀረቡት ቅሬታ በቀን 14/04/2015 ዓ.ም ፤ እንዲሁም የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 242253 ያቀረቡት ቅሬታ ተመርምሮ በቀን 06/07/2015 ዓ.ም ውደቅ ተደርጓል። ስለሆነም አመልካች የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያሳለፈውን ውሳኔ ማስለወጥ ሳይችሉ ቀርተዋል።

በሌላ በኩል 2ኛ ተጠሪ የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ ተቃውሞ በበኩሉ ለፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ይግባኝ ላይ ከአመልካች ጋር በመ/ቁ 281024 ተከራክረው በቀን 03/10/2024 ዓ.ም በዋለ ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም ተብሎ ፀንቷል። 2ኛ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ የሰበር አቤቱታ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ከአመልካች ጋር ክርክር አድርገው በሰ/መ/ቁ 231676 በቀን 24/08/2015 ዓ.ም በዋለ ችሎት ውሳኔው ጸንቷል።

አመልካች እንዲፈፀምላቸው የሚጠይቁት የፍ/ባለመብት ያደረገኝ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሳይሻር እስከ ሰበር ደርሶ ፀንቷል በሚል ሲሆን 1ኛ ተጠሪ በበኩሉ የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ ይግባኝ ብሎ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ያሻረው በመሆኑና በዚህ ላይ አመልካች ቅሬታቸውን ለጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝና በሰበር አቅርበው አያስቀርብም ተብሎ የፀና በመሆኑ፤ የሰበር አጣሪ ችሎቱ አያስቀርብም ማለቱ በውጤቱ ባለ አምስቱ ሰበር ችሎት በጉዳዩ ላይ ከሚሰጠው ውሳኔ የሚለይ ባለመሆኑ ሊፈፀም የሚችል ውሳኔ የለም፤ እንዲሁም በሁለቱም የይግባኝ መዝገቦች የአሁን አመልካች መ/ሰጪ ስለነበር መዛግብቱን ማጣመር ይቻል ነበር፤ ቀድመን የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ያሻርነው እኛ ነን ስለዚህ ውሳኔው ሊፈጸም አይችልም በማለት ተከራክሯል።

የአፈጻጸም ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት በየደረጃው የተሰጡትን ውሳኔዎች ይዘት፤ ከሰበር ችሎት ማብራሪያ ጠይቆ የተሰጠውን ምላሽ እና የግራቀኙን ክርክር መርምሮ ለአፈጻፀም መነሻ የሆነው ውሳኔ በአንድ በኩል እስከ ፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ የጸና በመሆኑ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ይኸው ውሳኔ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ የተሻረ በመሆኑ አመልካች ይፈፀምልኝ የሚሉት ውሳኔ ሊፈጸም የሚችል አይደለም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል። በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ ግራቀኙን አከራክሮ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ ሰጥቷል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው። አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የስር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉት ውሳኔ ተሽሮ በፌ/መ/ደ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ 174822 የተሰጠው ውሳኔ ሊፈፀም ይገባል ተብሎ ውሳኔ እንዲሰጥ ጠይቀዋል። ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በ20/10/2016 ዓ.ም በዋለ ችሎት ጉዳዩ ከየትኛው የሰበር አስገዳጅ ውሳኔ ጋር በመቃረን የተወሰነ ስለመሆኑ ሳይጠቀስ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4)(ሸ) (የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ውሳኔ በመቃረን የተወሰነ ከሆነ ከሚለው) ጋር መታየት አለበት በሚል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት መርቷል።

ከፍሲል የጠቀስኩት የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን በሰበር ችሎት ጉዳዩ ሊታይ ይገባል ለማለት አስቀድሞ ተገቢ ምልከታ የሚሻዉ ነጥብ የሥር ፍርድ ቤት ለአፈጻፀም የቀረበውንና በተቃራኒ የተወሰነውን ፍርድ በማገናዘብ የሰጠዉ ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አለ ወይስ የለም የሚለዉ ነዉ።

በመሰረቱ ፍርድ የሚፈጸመዉ በፍርዱ ዓይነትና አኳኋን ስለመሆኑ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 378 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባል። የአፈጻጸም ክርክሩን የሚመራዉ ፍርድ ቤት የፍርድ ባለእዳዉን ጠርቶ ከመረመረ በኋላ እንደፍርዱ የማይፈጸምበት ምክንያት ያለመኖሩን ሲያረጋግጥ ብቻ ለአፈጻጸሙ ተስማሚ በሆነ መንገድ ፍርዱ እንዲፈጸም ትእዛዝ እንደሚሰጥ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህጉ አንቀጽ 386 እና 392/1/ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም ፍርድ እንዲያስፈጽም አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት አስቀድሞ እንዲመረምር የሚጠበቅበት መሰረታዊ ጉዳይ የሚፈጸም ፍርድ መኖር አለመኖሩን ነዉ።

በሌላ በኩል ከፍርድ አፈጻጸም ክርክር ጋር በተያያዘ ፍርድ ቤቱ እንዲፈጸም የቀረበለት ውሳኔ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ተሽሮ ከሆነ ይኸው በመሻር የተሰጠ ውሳኔ ስልጣን ባለው በበላይ ፍርድ ቤት እስካልተለወጠ ድረስ ሊፈጸም የሚችል ፍርድ እንደማይኖር ግንዛቤ

ሊወሰድበት የሚገባዉ ጉዳይ ነዉ። በፍርድ አፈጻጸም ክርክር የተሻረው ውሳኔ ዋጋ ኑሮት እንዲፈጸም ሊደረግ የሚችልበት የህግ ስርዓትም የለም። ከዚህም ሌላ የበላይ ፍርድ ቤቶች በሌላ የይግባኝ/የሰበር መስመር የቀረበላቸውን ክርክር መርምረው አስቀድሞ መሻሩ ሳይነገራቸው (ክርክር ሳይቀርብላቸው) በመቅረቱ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናት የሚሰጡት ውሳኔ በመሻር የተሰጠውንና እስከመጨረሻው ፍርድ ቤት ቀርቦ ያልተለወጠውን ውሳኔ ዋጋ የሚያሳጣ አይደለም።

በተያዘዉ ጉዳይ ከፍሲል እንደተገለፀው አመልካች ይፈፀምልኝ በማለት አቤቱታ ያቀረቡበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 174822 ነሐሴ 7/2013 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ለፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበው ይግባኝ መነሻነት ክርክር አድርገውበት በመ/ቁ 281023 ታህሳስ 13/2014 ዓ.ም በዋለ ችሎት አመልካች አከራካሪው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/1967 ያልተወረሰ ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ውድቅ ተደርጎ ይፈጸም የሚሉት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሯል። በዚህ ላይ አመልካች ይግባኝ ለፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ፤ እንዲሁም የሰበር አቤቱታ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቅርበው ውድቅ ተደርጎባቸዋል። በመሆኑም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የፍርድ ባለመብት ሆኜበታለሁ በማለት አፈጻፀም የሚጠይቁበትን ውሳኔ በመሻር ያሳለፈው ውሳኔ በበላይ ፍርድ ቤቶች ለማስለወጥ ሳይችሉ መቅረታቸውን ካረጋገጡ በኋላ የተሻረውን ውሳኔ ለማስፈፀም የሚያቀርቡት አቤቱታ ተቀባይነት የሚያገኝበት ይህ ነው የሚባል ምክንያት የለም። ጉዳዩ በመንግስት ተወርሶ ለረዥም ጊዜ ተጠሪ በሆኑት የመንግስት አካላት ዕጅ ይገኛል የተባለን ቤት የሚመለከት በመሆኑም ፍርዱን ተጠሪዎች ተነጣጥለው ሊፈጽሙት ይችላሉ የሚባልም አይደለም።

በመሆኑም የአፈጻፀም አቤቱታ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት አመልካች ይፈፀምልኝ የሚሉት ውሳኔ ሊፈጸም የሚችል አይደለም በማለት ያሳለፈው ትዕዛዝ በጉዳዩ ላይ የተሰጡትን ውሳኔዎች እና ለፍርድ አስፈጻሚ ፍርድ ቤት በስነስርዓት ህጉ የተሰጠዉን ስልጣን ያገናዘበ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት የለም።

የሰበር አጣሪ ችሎቱ ክርክሩ ከአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4)(ሸ) ጋር መታየት አለበት በሚል ጉዳዩን ለሰበር ችሎት የመራው ቢሆንም የተጠቀሰው ድንጋጌ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ውሳኔ በመቃረን ስለተሰጠ ውሳኔ የሚደነግግ በመሆኑና በተያዘው ጉዳይ ቅሬታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈው ትዕዛዝ ከየትኛውም የሰበር አስገዳጅ ትርጉም ጋር ይቃረናል የሚባል ባለመሆኑ በዚህ አግባብ መመራቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘሁትም።

በአጠቃላይ ቅሬታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በህጉ አግባብ የተሰጠ ነው ከሚባል በቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሰኝ ባለመሆኑ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 28(2) እና በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ-ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 7(1) መሰረት አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባ ነበር በሚል ስሜ በአንደኛው ተራ የተመዘገበኩ ዳኛ የሥራ ባልደረቦቼ ካሳለፉት ትዕዛዝ ተለይቻለሁ።

ፅ/ወ